# የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት(መኢአድ)፣ የሰማያዊ ፓርቲ(ሰማያዊ) እና የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ(ሸንጎ) በጋራ ለመሥራት ስላደረጉት ስምምነት የተሰጠ መግለጫ

ኢትዮጵያ አገራችን የረጅም ዘመን ታሪክ ካላቸው አገሮች አንዷ እንደመሁኗ የውጭ ወራሪዎችን ለመመከት ቆራጥ ልጆቿ በአንድነት በመቆም ነፃነቷ እንዳይደፈር ታግለው እንደሀገር አቆይተው ያስረከቡን አገር ነች። ሆኖም ከውጭ ጠላት ነፃነቷን ጠብቃ የኖረችው አገራችን በውስጥ አስተዳደር ከመጥፎ ወደ እጅግ በጣም መጥፎ አገዛዞች እየተሸጋገረች የኖረች አገር እንደሆነች እንገነዘባለን።

የሩቁን ትተን ባለፉት ሦስት አገዛዞች እንኳ ያደርሱት የነበረው የመብት ረገጣ ቀደምት አገራችንን ኋላቀሪ አድረጓታል፡፡ በተለይ አሁን ያለው አገዛዝ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን መጣስ ብቻ ሳይሆን ለ27 ዓመታት በተከተለው የቋንቋ ፌደራሊዝም ለዘመናት አብሮ የኖረውን ህዝብ እርስ በርሱ እያጋጨ አገራችን እዚህ ሁኔታ ላይ እንድትደርስ አድርጓታል፡፡ የገዢው ክፋት ብቻ ሳይሆን የተቃዋሚዎች አለመተባበርም ለአገራችን ወደዲሞክራሲ አለመሸጋገር ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡

እኛ መኢአድ፣ ሰማያዊ እና ሸንጎ ይህን በማጤን በኢትዮጵያ አንድነትና በዜጎች እኩልነት ከሚያምኑ ጋር የውስጥና የውጪ ድርጅቶች የሚለውን አጥር በመስበር፣ ከረጅም ጊዜ ምክክር በኋላ የየድርጅቶቹ ሥራ አስፈፃሚ ተወያይቶ ያፀደቀውን 4 ገፅ የመግባቢያ ሰነድ እና የፈቃደኝነት 3 ደብዳቤዎች መሠረት በማድረግ በአደረጃጀት፣ በፋይናንስ፣ በአቅም ግንባታ፣ በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ድጋፍ ማሰባሰብ፣ በብሔራዊ እርቅና መግባባት ጉዳዮችና በሌሎችም ፖለቲካዊ ተግባራት ላይ በጋራ ለመሥራት ተስማምተናል።

ይህ በጋራ ለመሥራት የተደረሰው ስምምነት ለሕዝባችን ጥያቄ ወቅታዊና ተጨባጭ ምላሽ የሚሰጥ በመሆኑ ኢትዮጵያውያን የትብብሩ አካል እንዲሆኑና አቅማቸው በሚፈቅደው ሁሉ ሁለንተናዊ ድጋፍ እንዲሰጡ ሦስቱም ድርጅቶች በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ዶ/ር በዛብህ ደምሴ | አቶ የሺዋስ አሰፋ | ዶ/ር ታዬ ዘገዬ |
| የመኢአድ ፕሬዘዳንት | የሰማያዊ ሊቀመንበር | የሸንጎ ሊቀመንበር |
| ፊርማ ________ 17/12/2017 | ፊርማ ________ 17-12-2017 | ፊርማ ________ 17-12-2017 |

ታህሣስ ፰ ቀን ፪ ሺህ ፲ ዓ. ም (December 17, 2017) ዋሽንግተን ዲሲ፣ ሰሜን አሜሪካ